# ራሣችንን እናታልል

ከዮዲት ገ. ( ሎዛን፣ ስዊዘርላንድ)

መቻቻል 3ኛ ዓመት ቁ.4 (የካቲት Feb.2002)

ብዙዎቻችን ስለ ሐገራችን ኢትዮጵያና ስለ ሕዝባችን ደካማ ጐን መስማትም ሆነ መናገር አንወድም። በእውነቱ ያሣምማል፣ እርስ በእርሣችን ግልፅ በሆነ መንገድ ያለውን ነገርና መሆን የሚገባውን ጉዳይ አንስተን አንነጋገርም። በተለይም ደግሞ የፖለቲካ ጥያቄ ካልሆነና ጣታችንን የምንቀስርበት ክፍል ካላገኘን በስተቀር! እኔ ግን ፖለቲከኞች ከሚያጠቁንና ከሚበድሉን ባላነሰ ሁናቴ ባሕላችን፣ ልምዳችንንና አስተሣሰባችን እንደበደለን ነው የሚሠማኝ።

ታዲያ ለምንድን ነው ይህንን በውስጤ የሚሯሯጠውን ቅሬታዬን ለአንባቢ የማላጋራው? ምናልባትም እናንተም ብተሆኑ እንደ እኔ በውስጣችሁ አስባችሁት ሊሆን ይችላል፣ ከዚህም አልፎ ተርፎ ከሚቀርባችሁ ሰው ጋር ተነጋግራችሁበትም ሊሆን ይችላል።

አብዛኞቻችን ሐገር ቤት በነበርንበት ጊዜ ስለ ሐገራችን ሲነገረን የምንሰማውና ለብዙ ጊዜያትም እንደ ተረትም ይሁን እንደ ታሪክ የሚዘከርልን፣ እናት ሐገራችን ኢትዮጵያ ለምለምና የዳቦ ቅርጫት እንደነበረች፣ አፍሪቃዊ የጥቁር አንበሣ እንደሆነች፣ በእንግዳ ተቀባይነቷና በአስተናጋጅነቷ ወደር እንደሌላት በአጠቃላይም እንደ ኢትዮጵያውያን ያለ ትሁትና ሰው አክባሪ እንደሌለ ነበር የሚነገረን። የሚነገረውም።

ይህ ብቻም ሣይሆን ኢትዮጵያዊነት ስሙ ብቻውን አኩሪ እንደሆነ ነበር ከትልቅ እስከ ትንሽ፣ ከተማረውም ወገን ይሁን ካልተማረው የሚሰነዘረው። «ያ» ማለት የቀድሞ አያት፣ ቅድመ-አያቶቻችን የሠሩት የታሪክ ውርስ እንጂ አሁን ባለው «አዲስ ትውልድ» (1) የተሠራ አንዳችም ነገር የለም።

ይህንንም ስል ኢትዮጵያዊነት በእርግጥም ከጋናዊነት ወይም ከቡርኪናፋሶነት አይበልጥም፣ አይሻልም። ግን ኢትዮጵያዊነት በdiaspora ጥቁሮች የሚታየው እንደ ጽዮን ነው። ያሉበትን ሐገር የሚያዩት እንደ ባቢሎን ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት ለነፃነታቸው ከሚታገሉ ሕዝቦች (ለካረቢያን ሕዝቦችና እና ለጥቁር አሜሪካኖች የ ( inspiration) ምንጭ ነው። ይህም በመሆኑ ከጋናዊነት በዚህ ረገድ ይለያል። በተጨማሪም ኢትዮጵያዊነት አፍሪቃዊነት ወይም ልንኮራበት የሚገባ ጥቁርነት ነው። የ«መሀሞ» መሥራቾች አዲስ አበባን የፖለቲካ መዲናቸው ያደረጉት እነዚህን ከግንዛቤ በመውሰድ ነው። ይህ ስለሆነ ግን ከሌላው የተሻልን ነን ማለት አይቻልም። ጋና፣ በነገሬ ላይ ፖርቱጋልን ለመቶ ዓመታት ያህል ገዝታ እንደነበር ታውቃላችሁ?

ይሁን እንጂ በድሮ ዝና ተኮፍሰን በመኖራችን አዲሱ ስማችንና መለያችን ለየት እያለ መምጣቱን መረዳት የሚሣነን እንደማንጠፋ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ኢትዮጵያ ማለት የረሀብ፣ የችግር፣ የጦርነት ... ተምሣሌት እየሆነች ባለችበት ወቅት ይህንን ስም በሥራ በመለወጥ ከመጣር ይልቅ ባረጀና ባፈጀ ዝና፣ በባዶ ቤት ተኮፍሰን ብንኮራና ብንኩራራ የዘመንና የትውልድ መሣለቂያ ከመሆን፣ ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር ለመጓዝና ፍሬውንም ለመቋደስ እንድንችል ለራሣችን የሚጠቅመንን አበጃጅተን በመገኘት ሐገራችንን መለወጥ ወይም ማበልፀግ ሲገባን በሄድንበት ቦታ ሁሉ እርስ

በራሣችን እየተሰባሰብን፤ ትተነው በመጣነው አጉልና ጐጂ ባሕል ተጠፍረን ከምንናቆር፤ በሐሜት መጥበሻ ላይ ከምንላወስ ይልቅ፤ እስቲ ለአንድ አፍታ እንኳን በትክክል ማሰብና ማቀድ ይኖርብናል ብለን፤ ሥራን ባሕል አድርገን፤ ታታሪዎችና ሞረለ-ጠንካራ ዜጋ ሆነን የዕድገት ደረጃችንን ከፍ ለማድረግ እንጣጣር። እኔ በበኩሌ ኢትዮጵያውያን «ፈረንጅ» መምሰል አለባቸው አልልም። ኢትዮጵያውያን እንጂ! የፈረንጅ ሥልጣኔ የቅጂ ሥልጣኔ እንጂ originality የለውም!! እንደ ንብ ከዚህም ከዚያም ቀሣስመው ያገኙትን «ሥልጣኔ» መቅዳት የለብንም። «monkey see, monkey do» የኛ አርማ አይደለም!

እኔ የሚታየኝ ይሄ ነው። አብዛኛውን ጊዜ አኗኗራችንና ውሎአችን እርስ በእርሣችን ነው። በራሣችንና በዙሪያችን ላይ የሽቦ አጥር የዘረጋን ነው የሚመስለው። በሰው ሐገር የሚኖር ሰው ከአካባቢው መማርና ፈጥኖም መረዳት ማህበራዊ ሁናቴ የሚያስገድደን ነው። ከአንድ ነጭ ዜጋ ጋር ስንገናኝ «የጥቁር ፈረንጅ ሆኖ ቀለሙን ቀይሯል» እንላለን። ከአንድ አፍሪቃዊ ሰው ጋር ግንኙነት ያደረግን ከሆነ ደግሞ «ከባሪያ ጋር መወዳጀት» ይባላል። ይህ ሁሉ አስተያየት የማህበራዊ በይነ-ግብርን እሴት ካለመረዳት የሚመነጭ የአስተሣሰብ ድክመት ሊሆን ይችላል። በተለያዩ ምክንያቶች ሐገራችንን ለቅቀን የወጣን እንደመሆናችን የምንኖርበትን አገር ባሕልና የአኗኗር ዘይቤ በማጤን፤ ኑሮን በዘዴና በብልሃት መምራት ለእኔ አንድ ጥበብ ነው። እስኪ አስቡት ... አንድ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ የውጭ ዜጋ ሁልጊዜ በትላልቅ ሆቴሎችና አካባቢዎች ከአገሩ ዜጐች ጋር የሚውለውን ሰው ነው የምናደንቀው ወይስ ... ከኢትዮጵያውያኖች ጋር ለመዋል ጥረት የሚያደርገውን?፤ እንጀራችንን አድንቆ የሚመገብልንን እና ቋንቋችንን ለመናገር የሚሞክረውን???

መልሱ ግልፅ ይመስለኛል። ይኼ ደግሞ የአዳም ልጆች ፀባይ ነው። እኛነታችንን እናደንቃለን፤ እንወዳለንም።

ከላይ ጠቆም ያደረግሁትን የትህትና ጉዳይ በሚመለከት፤ ከነበሩን ውብ ባሕሎች አንዱ ትህትና እንደነበር ተጠቅሷል። በዚህ ትውልድ ላይ የሚንፀባረቁት ባህሪያት ደግሞ ለየት ይላሉ። በዚህ ምክንያት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ማንሣትና መልሣቸውንም ማሰላሰል ተገቢ ይመስለኛል። በእርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን ትሁቶች ነን? ለመሆኑ ትህትና ምንድን ነው? ሰውን ሁሉ ማክበር ወይስ እየመረጡ? አንድን ሰው ትሁት ነው የምንለው በፊት ለፊት በጥሩ ቋንቋ ወይም ምላስ አነጋግሮን ከጀርባችን ግን ቆርጦ ስለቀጠለን ይሆን? ትህትና የሚሰራው በዕድሜ ገደብ ነው? ትንንሾች ታላላቆቻቸውን ወይም ሽማግሌዎችን ያከብራሉ። በተራቸው ትናንሾችንስ ማን ነው የሚያከብራቸው? እንደገና ታናናሾቻቸው? ለምን ትህትናችን እኩል አይሆንም? ለምንስ ትልቅ ትንሹን፤ ትንሽ ትልቁን አያከብርም? ለምን አንድ የውጪ ዜጋ ፊት የምናሣየውን ትህትና ዓይነት ለኢትዮጵያዊው ወገናችን አናሣየውም? እንግዲህ ይህን ሁሉ ስል በዓይነ-ሕሊናዬ የማየው አዲስ አበባን ነው። ምክንያቱም የኖርኩትም፤ ያደግሁትም፤ የማውቀውም አዲስ አበባን ብቻ ነው። ታዲያ ... አዲስ አበባን ብቻ መሠረት አድርጋ ስለ ኢትዮጵያ እንዴት ታነሣለች ትሉኝ ይሆናል። በመሠረቱ መዲናዋን በመቃኘት ብቻ «ኢትዮጵያ» ማለት ምን ማለት እንደሆነ መናገር አስቸጋሪ ብቻም ሣይሆን የማይቻልም ነው። እኔ እንደሚሰማኝ የውጪ ዜጐች ስለ ኢትዮጵያ የሚወስዱት የመጀመሪያ impression አዲስ አበባን እንደረገጡ ይመስለኛል። አብዛኛው የተማረ ሰውም ሆነ ልዩ ልዩ ተቋማት የሚገኙት በዋናው ከተማችን ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ለማንኛውም ዲፕሎማሲያዊ ወይም ዓለም-አቀፍ ግንኙነት አስተዋጽዖ የሚያደርገው ክፍል ማለት ነው። ታዲያ እንግዲህ ምን እናድርግ? በኢትዮጵያዊነታችን እንመፃደቅ? አዎን እንጂ!!!

«እግዚአብሔር ኢትዮጵያውያንን እጁን ታጥቦ ነው የሠራን። ከነጩም ከጥቁሩም የበለጥን ነን» የምንል ጥቂቶች አይደለንም። «አዲስ አባባ ገነት ነች» ስንልም የምንደመጥ ላንጠፋ እንችላለን።

እውነት አዲስ አበባ ገነት ነች? አዲስ አበባ ለኔ ገነት አይደለችም። ከማንኛውም የሐገራችን ክፍሎች ወይም ክልሎች በበለጠ ሁናቴ ባሕላችን የጠፋበት፣ ችግር፣ ረሀብ፣ ሥራ-አጥነት የበዛበት፣ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት የፈሉበት፣ የሕዝቡ ተስፋ መቁረጥ በኑሮው ላይ እንዲማረር ከዚያም አልፎ ከእሱ የተሻለ ኑሮ ያለው ላይ ሁሉ ከባድ ጥላቻ የሚያሣይበት፣ ጉደኛ ከተማ ነው። የሰቆቃ ከተማ!

የተነሣሁበትን ርዕስ ስጀምር ከፖለቲከኞች ባላነሰ ሁናቴ ባሕላችንና ልምዳችን ይጐዳናል፣ ያልኩበት ዋናው ምክንያት ይኼው ነው። «እኛ ትልቆች ነን» በሚል ተኮፍሰን ትህትናን ረሣናት። እኛ ከሌላው የተሻልን ነን እያልን እራሣችንን ስናታልል ከሌላው ያነስንበትን ሰባራ መጠገን አቃተን።

ህፃናት ልጆች በአሻንጉሊት መጫዎቻ ዕድሜያቸው ብሎም በመማሪያ ጊዜያቸው በችግር ምክንያት ከመንገድ ወጥተው ሲንከራተቱ እናያለን። አዲስ አበባ ገነት አይደለችም። ግን ሲኦል ... እንጃ! ወደዚያው እያመራች ሣይሆን አይቀርም።

በእኔ ግምትና አስተያየት መፍትሄ የሚመስለኝ በአጉል መመፃደቅ፣ በባዶ ኩራት፣ በሌለንና በባዶ ኪሣችን፣ ከአቅማችን በላይ መንጠራራቱን ትተን፣ የተነፋውን ልባችንን አስተንፍሰን ዕውቀታችንንና ጉልበታችንን አስተባብረን፣ የሚያውቅ ላላወቀ ወንድሙ የሚያሣውቅበት፣ ጠንካራው ደካማውን የሚያግዝበት ... ሁናቴ ተፈጥሮ ይህች በኤኮኖሚና በፖለቲካ የደቀቀች ሐገራችንን ከተዘፈቀችበት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት፣ እራሣችንን ለማዳን ዋነኛ መፍትሔ ገበናችንን መደባበቅ ወይም መሸፋፈን ሣይሆን ይልቁንም እውነትን በግልጥ አስቀምጠ፣ ችግሮቻችንን በጥሞና በመረዳት የጋራ የመፍትሄ ሃሣብ ለማፍለቅ ስልት መቀየስን የመሰለ ፍቱን መድሃኒት አይገኝም። መመካከር ደግ ነው።

እስቲ ለአንድ አፍታ እናስብ፣ ለአንድ ሕመምተኛ ሰው በሽታው ምን እንደሆነ ሣይታወቅ መድሃኒት ይገኝለታል እንዴ? ሐኪሙ ምርመራውን የሚጀምረው በሽታው ምን እንደሆነ ለማወቅ አይደለም እንዴ? የእኛስ በሽታ የድህነታችን፣ የኋላ ቀርነታችን የሌላም የሌላም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተጠንቷል? እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ የእኛ አንዱ ትልቁ በሽታችን ኩራት ነው። ባዶ ኩራት! አበሻ ከነጭ፣ ትግራይ ከጉራጌ፣ አማራ ከኦሮሞ፣ የተሻለ ፍጡር ነው እያልን ጊዜያችንን እናቃጥላለን። ባዶ ኩራት፣ ባዶ ክርክር፣ ማንም ከማንም አይበልጥም በፍጡርነቱ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዱ ከሌላው ማነሱን በሥራው ውጤት ያሣያል። እኛ ከሌላው ብንበልጥ ኖሮ ረሀብና እርዛት እንዲሁም እንግልት አይደርስብንም ነበር። እቤታችን የሻማ ጭላንጭል የመሠለ መብራት አይኖረንም ነበር። (እሱም የሌለው አለ!) እኛ ከሌላው ዓለም ሁሉ በድህነታችን ወደ ታች ያቆለቆልን መሆኑ አጠያያቂና አከራካሪ አይደለም። ታዲያ ሃብታም ነን እያልን እራሣችንን አናታልል። ይልቁንስ ድህነታችንን አውቀን ተግተን እንስራ። ተስፋ ለቆረጠው ሕዝባችን ተስፋ እንሁነው።

ትላንት አልፏል። ነገን ግን ምን ልናስመስለው እንደተዘጋጀን ለማየት ጓግቶ ይጠብቀናልና። ነገን የተስፋ፣ የዕድገት፣ የእርቅ፣ የሠላም ቀን እናድርገው ወይስ የጥላቻ፣ የመናቆር፣ የሃሜት፣ የወቀሣ፣ የጥል፣ የጦርነትና የእልቂት? ... ወዘተ. ወዘተ.

እኔ በበኩሌ ብዙ የሚጠብቁኝ ተግባሮች መኖራቸውን አውቄ ለማደግ፣ ድህነቴን ለመቅረፍና ለመበልፀግ፣ አንገቴን ደፍቼ ሥራዬ ላይ ልትጋ ባይ ነኝ። እናንተስ? PPP

<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>፣

(1) እዚህ ላይ አንባቢያን ሊያሰምሩበት የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ቢኖር፣ አዲሱ ትውልድ የነዮፍታሔ ንጉሤ፣ የአበራ ገሙ፣ የዘርዓይ ደረስ፣ የጥላሁን ግዛው፣ የዋለልኝ መኮንን፣ የማርታ መብራቱና የነብርሃነ-መስቀል ትውልድ ከሆነ ብዙ ቁም ነገሮችን ሠርቶ ማለፉን ነው። ይሁንና የፋፋ «generation» ቢሆን በዘመነ-ደርግም ሆነ አሁን እየተጋደለ ነው። በየሰበብ አስባቡ (pretexte ጭምር) ከሐገር የወጣው ግን ይህን ያህል ፋይዳ ያለው ሥራ ሲሰራ አይታይም።